# በሳውዲ አረቢያ የኢትዮጵያውያ መከራ !
# የተደበቁ እውነቶች ! ክፍል አራት

ነቢዩ ሲራክ- ከሳውዲ አረቢያ

## የጂዳ ማህበረሰብና የመምህር ""ትራንስፎርሜሺን"" ህልም. . .

በሳውዲ የኢትዮጵያውያን ሮሮ - የተደበቁ እውነቶች ብየ በጀመርኩት ወጋወግ ዙሪያ ሆኗልና የሚቀድም የሚሰልሰውን አወጣለሁ አወርዳለሁ. . . መስከረም በጠባ ማግስት ሌላው ቢቀር ከሮመዳን ዋዜማ ተጀምሮ በቀጠሉት ቀናት መከራው የጸናባቸውን ወገኖች ውሎ አዳር ለማስቃኘት መጀመሬ እውነት ነው ! በሶስተኛ ክፍል መጣጥፌ ካነሳሁት ሮሮ ጋር በተያያዘ ኢትዮጵያውያን ታሳሪዎች በመሩት የእስር ቤት ሰበራ የወጋወጌን አቅጣጫየን ለመቀየር መገደዴ የሚዘነጋ አይሆንም. . . ያ ትናንት ነበር !

ዛሬም ቢሆን እንደ ትናንት የጀመርኩትን መንገድ የሚያስቀይር ሰበር የተደበቀ እውነት ምልከታን የሚያጎላ ሰሞነኛ የወሬ ጋሬጣ አላጣሁም፡፡ . . . የዛሬው ምክንያት በችግር ዳፋ ላይ በሚገኘው በጂዳ ማህበረሰብ ስም የተነገረ ተአማኒነት የሌለው ዜና ነው፡፡ ተናጋሪው በሳውዲ አረቢያ ለበርካታ አመታት ቢኖሩም ከአመት ላላነሰ ጊዜ በጂዳና አካባቢው ታይተው የማያውቁ ወንድም ናቸው፡፡ ለጉዳዩ ቅርበት ያለን ወገኖች እኒህ ለግላጋ አንደበተ ርቱዕ ወንድም የምናውቃቸው በትግራይ ልማት ማህበር መሪነታቸውም ቢሆንም ስማቸው የሚነሳው ግን የቪዛ ነጋዴ መሆናቸውን ነው፡፡ ባንድ ወቅት በደራው የቪዛ ነጋዴ ከተለያዩ ወገኖች ተከሰው ደርዘን የሞሉ የገንዘብ ክስ የተመሰረተባቸው እርግጥ ነው፡፡ በሺዎች የሚቆጠሩ ዜጎች በመከራ ላይ በወደቁበት ሰአትና እነሱን ለመታደግ ርብርብ በሚጠየቅበት ወቅት ባልተጨበጠ እውነታ ከአመት በላይ ስላሰናበታቸው ስለጂዳ ኮሚኒቲና እርሳቸውን ስለገባቸው "ትራንስፎርሜሺን" በቴሌቪዥን ማስነገራቸው በእርግጥም የሰማውን ነዋሪ አንገበግቦታል፡፡ ካለፉት ጥቂት ወራት ወዲህ ግን ከከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣናት ጋር ያላቸውን ቅርበት ተከትሎ በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን መስኮት በተደጋጋሚ እናያቸው ይዘናል፡፡ ከፓርላማ መከፈቻ እስከ መጽሃፍ ምረቃ በሁሉም ቦታ የመታየታቸው አቅጣጫ "የመተካካቱ" አካል ሆነው ጉብ እንዳይሉበት የጂዳው ወገን ቢሰጋ አይፈረድበትም ፡፡ በርካታዎች "መምህር ትልቅ ስህተት ተሳሳቱ ! . . . ብለው ብለው በትራንስፎርሜሺን መጡብን፤ አቤት የሰው ነገር መቸም ቀዳዳ ሲፈለግ ውሎ ቢያድር ያውም በዚህ ወቅት እንዲህ ያለ ስራ ባልተገባ ! " ሲሉ አስነዋሪ ቃላትን ላለመናገር ቃላት መርጠው የሚናገሩትን ጨምሮ " ድሮስ ቢሆን . . . " እያሉ የውስጥ ገመናን የሚያወጡት ወገኖች ውርጅብኞቻቸውን ማውረድ የጀመሩት ማታ ዜናው ተሰምቶ እንዳበቃ ነበር፡፡ በርካታ ወገኖች ሁኔታውን በአግራሞት ከመመልከት አልፈው መምህሩ ሲናገሩ ምንጫቸው ምን እንደሆነ የማይጠይቁ የቴሌቪዥን ሃላፊዎችን ጨምሮ በጋዜጠኞች የተሰማቸውን ቅሬታ በመግለጽ ላይ ናቸው፡፡ የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ያቀረባቸው ወንድም በመካከለኛው ምስራቅ የትግራይ ልማት ማህበር ከፍተኛ ሃላፊ የጂዳ ኮሚኒቲ የህዝብ ግንኙነትና ምክትል ጸሃፊነት መባረራቸው የታወቀ ሆኖ ሳለ እንደለመዱት በሌሉበት ቦታ የሌለ ታሪክ እያነሱ ሲጥሉ ሰምቻለሁና ነው፡፡ ድሮ ድሮ እንደፈለጉ በፈለጉት ሰአት በሚቀርቡበት የመንግስት ሚዲያ ከሃቅም የራቀ ቢሆን ስለ ትምህርት ቤቱ ፤ስለ ኮሚኒቲውና ስለተለያዩ ማህበራዊ ጉዳዮች ሲናገሩ እድሉን በሚሰጡዋቸው ጓዶቻቸው አዘንን፡፡ የመምህር የሰሞኑ ስራ በተደጋጋሚ የተከሰሱባቸውን የእምነት ማጉደል የክስ ዶሴ የሚዘጋ ሊሆን አይችልም፡፡ ክሱ በኮሚኒቲና በቆንስል መስሪያ ቤቱ በድብስብስና ግልጽ ባልሆነ መንገድ ቢዘጋም እንባቸውን የሚያዘሩትን ዜጎች እያቀረብን ሃቁን ተቀበሉ እያልን ልሞግታቸው ሞራል ከዶናልንና ይህ አይሆንም፡፡ በሌለ ነገር በተገፊው ማህበረሰብ ስም ስለሚናገሩት "የህግ ያለህ!" ልንላቸው ይገባል ባዩ ከነዋሪው አልፎ የድርጂት ጉዋዶቻቸው አቁዋም እየሆነ መምጣቱ ተመልክቷል . . መምህር አላዎቁትም እንጂ ኮሚኒቱ ጥርሱን የፈጀ አንበሳ ከሆነብን ከራርመናል ! በ"ትራንስፎርሜሺን" ዙሪያ የደሰኮሩለት ማህበር እርሳቸው በሃላፊነት በነበሩበት ጊዜ ጀምሮ እየተሸመደመደ ትልቅ ስሙን ይዞ ባልረባባ ስራ ሲውተፈተው ለመክረሙ መምህር አቡዋድነው የሰገሰጉዋቸው የፓሪቲ አባላት ተጠያቂ ናቸው ባንልም ማህበሩ እንዲዳከም ምክንያት ለመሆኑ ይጠፋቸዋል አልልም ፡፡ ኮሚኒቲው በብቸኝነት የሚነሳበት ትምህርት ቤትም ቢሆን የከረመው አበሳውን ሲያይ ነው፡፡ በቅርቡ እየወሰደ ያለው የመስፋፋት እርምጃ እሰየው ቢያሰኝም የተቸገሩ ወገኖችን በመደገፉም ሆነ ድምጻቸው የሚሰማበትን መንገድ በማፈላለጉ ረገድ እስካሁን የሰራ ስራ በጉልህ አልታየም፡፡ በተለይም የጂዳን አካባቢው ነዋሪ ኢትዮጵያውያኑ እስር ቤት ሰብረው አመለጡ ከተባለበት ቀን አንስቶ ህገወጦችን ለመያዝ በሚል ያለ ፍርድ ቤት ትእዛዝ የሰለማዊ ነዋሪው ቤት በመሰበርና በየቀዳዳው በሚደረገው ፍተሻ ህጋዊው ነዋሪ ሳይቀር የሚያደርገው ጠፍቶች በመሰቃየት ላይ ይገኛል፡፡ ታዲያ ኮሚኒቲው የማህበሩ ችግር ተመልክቶ ማድረግ እንኳን ባይችል ችግሮችን ለሚመለከተው የቆንስል መሰሪያ ቤት ያሳወቀበት ሁኔታ የለም፡፡ እንግዲህ መሰል

**pdfMachine**
**A pdf writer that produces quality PDF files with ease!**
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, simply open the document you want to convert, click “print”, select the “Broadgun pdfMachine printer” and that’s it! Get yours now!

ችግር ከላያችን ላይ ባለበት ሁኔታ እንኳንስ ኮሚኒቲው ጉዳዩ በቀዳሚነት የሚመለከተው ቆንስል መስሪያ ቤት ሃላፊዎች እንኳ ስለ"ትራንስፎርሜሺኑ" ጉዳዩን ማንሳት አልዳዳቸውም፡፡

"በዚህ ፈታኝ ወቅት ለጂዳና አካባቢው ነዋሪ መንግስት ድጋፍ ያደርግ ዘንድ አቤት ከማለት ባሻገር በነዋሪው ስም የፖለቲካ ፍጆታ ዲስኩር መደስኮርዎን ያቁሙ ! እባክዎን በስማችን የማይሆነውን አይናገሩ" በሚል በሚሰነዘረው የህዝብ አስተያየት ጆሮ ሊሰጠው የሚገባ ሃቅ ነውና መልስ በመስጠቱና አስተያየቱ በማቅረቡ ረገድ ስራን ብሰራ ደስ ባለኝ ነበር . . . ! ይህ ሁኔታ የተደበቁ እውነቶች ዳሰሳየ አካል በማድረግ መልስ መስጠቱን ግን አሁንም ቀልቤ ይሻዋል፡፡ . . . የመጣጥፌን ርዕስ "የጂዳ ኮሚኒቲና የመምህር ያሲን ራጁ ትራንስፎርሜሽን" አልኩና ጀመርኩት ፡፡ እናም መምህር ያሲን ራጁ ይህንን ወሬ የትና ለምን እንደፈበረኩት አልገባኝምና ! በዚህ ሁኔታ ርዕስ አውጥቸ መልስ ቢጤ ለመስጠት ከጀልኩና የሮመዳን ወጌን እንዳያቆረፍደው በመፍራት በቀጣይ ለመዳሰስ በቀጠሮ አለፍኩት! ይህንና ያንን ሳወጣ ሳወርድ ብዙ ጊዜ ፈጀሁ መሰል አይኖቸን በርቀት ተክየ ከሄድኩበት እሰጣ ገባ ስመለስ ከተንጣለለው ባህር ላይ የሚፍለቀለቀው ደመና የማይጠጋው ደንጋዛ ሰማይ የሚበተነው የብርሃን ነጸብራቅና ሰማዩ እየጋለ በመሄዱ በግርማው እንደተኮፈሰ ሳላውቀው ጠፍቷል . . .

የባህሩ ውበት ሸሺተውት አገኘሁት . . . ለካስ ሰአቱ ሄዷል . . . ሩቅ ሄጀ ያሰብኩት ያወጣሁ ያወረድኩትን አብሰልስየ በደረስኩበት ውሳኔ ለመጽናት ወሰንኩ . . . ደግሞ በክፍል ሁለት ቅኝቴ ያቆምኩበት የረመዳን ዋዜማ የድልድይ ስር ትዕይንት ተጀመረ እንጂ አላበቃም ... እናም በዚያ ላይ ትኩርት መስጠት ተገቢ መሆኑን ደጋግሜ ለራሴን አስረዳሁ . . . እናም ወደ ቢሮየ ገሰገስኩ . . .

## "የካፍቴሪያው አንበሶች" ና ባለ ጊዜ ካድሬዎች . . .

ሮመዳን የቀሩት ሁለት ቀናቶች ብቻ ናቸው፡፡ በቆንስሉ በር የተሰበሰቡት ዜጎች በሙቀቱ ተማረዋል፡፡ ወደ ቆንስሉ ጎራ የሚሉ ባጉዳዮች ከቅርብ ርቀት ከሚገኙት የኮሚኒቲ ካፍቴርያ ቀዝቃዛ ውሃ እያመጡ ያቀርቡላቸዋል፡፡ እኔን ጨምሮ አንዳንድ ወላጆች ልጆቻቸውን ወደ ትምህርት ቤት አድርሰው በአካባቢው ስራ ያላቸው ጎልማሶች ቁርስ ለመብላትና ማኪያቶዋን ለመቀማመስ በኮሚኒቲ ካፍቴርያ ብዙ ጊዜ ስለማይጠፉ የካፍቴሪያው የዘወትር ደንበኞች ሆነናል፡፡ ብዙውን ጊዜ ክብ ክብ ሰርተን እንቀመጥና የዋለ ያደረውን ወሬ እንደቁሳለን፡፡ የኮሚኒቲው ካፍቴሪያ በተለያዩ ጠረጴዛዎች ላይ የተሰበሰቡት ሁሉም የተለያየ ቃና ያለውን ወሬ እስካፍንጫው የሚወራበት ቦታ ሆኗል፡፡ በአንዳንዱ ጠረጴዛ ላይ ከሚሰባሰቡት የፖለቲካና የልማት ማህበራት ስለሚያወሩት አይፈሩም፡፡ ከድንበር ባያልፉም የሚያራምዱትን የፓለቲካ አቋዋም በነጻነት ይጫወታሉ፡፡ የፈለጉትን ማስፈጸም ይችላሉ፡፡ አሁን አሁንማ ደግሞ ሹመቱ የነሱ ብቻ ሆኗል መባሉ ሃሜት አልሆነም፡፡ ዲፕሎማቶች መብት ጥበቃውን አላልተው ፓርቲን በማደራጀቱ ላይ ጠንክረው ስለገፉበት ይመስላል ትንሺ የነበሩት ዛሬ ወደ አራት መቶ ተጠግተዋል ይባላል፡፡ በማህበረሰቡ ችግር ዙሪያ ግን መፍትሄ ሲያፈላልጉም ሆነ በቆንስላውን መስሪያ ቤት ላይ የሰላ ሂስ የሰጠ "ተቃዋሚ " እያሉ ስሙን ያበዙበታል. . . ይከታተሉታልም፡፡

"አሺሙዋጣጮች" "የካፍቴሪያ አንበሶች" እያሉ በሹክሹክታ ስም የለጠፉባቸው ወንድሞች ስብስብም ካፍቴሪያው ከሚያደምቁት መካከል የሚጠቀሱት ናቸው፡፡ እኒህኞቹ ጸጉረ ልውጥ ወይም ነባር ካርዴ ካዩ ወጉን አይዳፈሩትም፡፡ ነጻ የሆነ ሰው ሲያገኙ ግን የሚወራውን ቁምነገር ማሰሪያ የለውም እንጂ ጠቃሚና ተፈላጊ ሳይሆን አልቀረም፡፡ አንድ ቀን ሻሂ ልጠጣ ከመግባቴ ባንኮኒ ላይ ሆኘ አስተናጋጁን አዘዝኩ፡፡ የት ነው የምትቀመጠው ከ"የካፍቴሪያ አንበሶች" ጋር ነው ወይስ "ከመተካካቶች" ጋር ሲል ያላገጠው ልቆጣጠረው የማልችለው ደረጃ አሳቀኝ፡፡ አስተናጋጁ ወዳጀን ምነው ይህን ስም ለጠፍክባቸው ሳልለው አልቀረሁም፡፡ "እንዲህ የተባሉት ያለ ነገር አይደለም" አለኝና ያዘዝኩትን ሻሂ ባንኮኒ ተደግፌ እስክጠጣ አጫወተኝ . . . ምክንያቱን ደረደረልኝ. . . ከውጭና ከሃገር ውስጥ ፖለቲካ እስከ ጉዋዳ ጉድጉዋዳ ማህበራዊ ኖሮ ወግ ከመሰለቅ አልፈው ምራቅ የሚያስውጡ ድንቅ ወሬወችን ያወራሉ፡፡ መላ ምታቸው የተጨበጠን ያህል ያስደስታል፡፡ ታዲያ ምን ዋጋ አለው . . . ፖለቲካውን ቢጠሉት በማህበራዊ ጉዳይ ስብሰባ ተገኝተው ስለማህበረሰቡ መብት ድምጻቸውን አለማሰማታቸው ብቻም ሳይሆን ጭራሺ አለመገኘታቸው ፡፡ በትምህርት በቱ ጉዳይ በካፍቴሪያ ጤረጴዛ ዙሪያ ቢመክሩ ቢዘክሩም በስብሰባ ላይ ተገኘተው ሃሳብ ስለማይሰጡ ይህ ስም እንደተሰጣቸውና ወሬያቸው ጉንጭ ማልፋት ብቻ በመሆኑ "የካፍቴሪያ አንበሶች" የሚል ቅጽል ስም እንደተሰጣቸው ሲያወጋኝ ፈገግ አሰኘኝ፡፡ ይህ የኔም ትዝብት ነበርና ሲጀመር የኮረኮሩኝን ያህል አስቆ በ"አሺሙዋጣጮች" ስም አሰጣጥ አስደመመኝ፡፡ ገና ስደተኞች በቆንስሉ በር አመጽ አነሱ ሲባል " የነእንቶኔ

**pdfMachine**
**A pdf writer that produces quality PDF files with ease!**
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, simply open the document you want to convert, click “print”, select the “Broadgun pdfMachine printer” and that’s it! Get yours now!

ሰልፈኞች" እያሉ በወገናቸው ዙሪያ ይሳለቃሉ ሲባል ብሰማም ይህን ሰሞን "የካፍቴሪያ አንበሶች" ወኔ ያለው የተቆርቋሪነት ስሜት ለችግረኞች ምግብና ውሃ የማቅረባቸውን ተመልክቻለሁ፡፡ ካሳዩት ሰብዕና ባልተናነሰም ባደረጉት በጂዳ ኮሚኒቲ ባለስልጣናት ላይ ያደረጉት ጫና ቀላል አልሆነም፡፡ የኮሚኒቲ ሃላፊዎች በዜጎች ችግር ዙሪያ የቆንስል ሃላፊዎች ጋር ለመምከር ምሺት እንዲቀመጡ ምክንያት ሆነዋል፡፡ ዳሩ ግና የኮሚኒቲ ሃላፊዎች ከተገፊዎች ጋር ያካሄዱት ሺምግልና አይሉት ምክክር ህግን ተንተርሰውና መብታቸውን ሊያስከብሩላቸው ቀርቶ በህዝብ ከተሰራው መጠለያ የታመሙትና የደከሙት እንዲያርፉ ማድረግ ተስኗቸው ቀርቷል፡፡

## የስልኩ ጥሪ . . .

የቢሮ ስራየን ጨራርሸ ረፋዱ ማስታወሻየን ለመያዝ ቡናየን ፉት እያልኩ አንድ ሁለት ማለት ስጀምር የስልክ ጥሪ ደረሰኝ፡፡ የማውቀው ቁጥር ቢሆንም የማን እንደሆነ መለየት ግን አልቻልኩም፡፡ የተደወለልኝ በተንቀሳቃሺ ስልክ አይደለምና ብዙ ጊዜ ውርጂብኝ የምሰማው በቤት ስልክ በመሆኑ ያው ስድቡ ነው አልኩና ራሴን የመጣውን ለመቀበል አዘጋጀሁና ስልኬን አነሳሁ . . .

"አቶ ነብዩ ነህ . . . "

አዎ ማልበል የኔ እመቤት

" ከቆንስላ ጽህፈት ቤት ነው አቶ . . . ሊያነጋግሩህ ይፈልጋሉ፡፡" የመስሪያ ቤቱ ኦፐሬተር

" አቶ ነቢዩ ..."

አቤት ማን ልበል . .

"ከቆንስል ጽህፈት ቤት ነው፡፡ . . . እባላለሁ ፡፡ በአንድ ጉዳይ ለመመካከር ፈልገንህ ነበር፡፡"

በምን ዙሪያ ነው ፡፡ ጉዳዩ ማወቅ እችላለሁ?

" አይ. . . እንደምታውቀው የቆንስል መስሪያ ቤቱ በዜግነት ጉዳይ ከዜጎቹ ጋር ይነጋገራል፡፡ አንተም ዜጋ እንደመሆንም በአንዳንድ ጉዳይ ለማነጋገር ያህል ነው ፡፡" አሉኝና ሳላቅማማ ወደ ቆንስል መስሪያ ቤቱ አመራሁ፡፡ ሰአቱ ወደ አራት ሰአት ገደማ ሆኗል፡፡ በቆንስሉ በር የተኮለኮሉት ዜጎች ቁራጭ ካርቶችን በጅ በጃቸው ይዘው እያረገቡ ተጋድመዋል፡፡ ሙቀቱን ያልቻሉት ህጻናትና በበሺታ የተዳከሙትን ሙቀታቸውን ለማብረድ የፈቀደ ሁሉ ካርቶን ቆረጥ እያደረገ ያርገበግብላቸዋል፡፡ በአንጻሩ ጉዳዩን ለማስፈጸም የመጣ ኢትዮጵያዊም ሆነ ቪዛ ለመውሰድ የሚመጡ ወገኖች ቆም እያሉ ግራ የሚያጋባውን ሁኔታ ለማወቅ ጀሮዋቸውን አቅንተው ጠይቀው ለመረዳት ይሞክራሉ፡፡ አንዳንዶች ውሃና ምግብም እየገዙ ያመጡላቸዋል፡፡ እኔም እንደነሱ አዳራቸውን ጠጋ ብየ ጠየቅኩና ወደ ቆንስሉ በር ተጠጋሁ፡፡ በሩ ተዘግቷል፡፡ ምነው ያለ ወትሮው ? አልኩት የቀድሞ አነጣጣሪ ተኩዋሺ ነበር በመባል የሚወደሰውን ታጋይ የቆንስል ጸጥታ አስከባሪ፡፡ በትንሽ ከብ ፊቱ ላይ የሚደፋውን ትልቅ ጥቁር መነጽር እያሻሸ . . . "ምን ይደረግ ተመልከተው. . . " ሲል በበሩ የተለጠፈውን ማስታወቂያ አመላከተኝ፡፡ አነበብኩት፡፡ ማንኛውም ባለጉዳይ ጉዳዩን ተናግሮ መታወቂያ እያሳየ መግባት እንዳለበት አዲስ ትዕዛዝ መተላለፉን ተረዳሁ፡፡ የተጠራሁበት በዜጎች ደህንነት ቢሮ በኩል እንደሆነ መግለጼ የግድ ነው ለምግባት . . . እናም ተደውሎ ተጠየቀና እንድገባ ተፈቀደልኝ፡፡ ባልስልጣኑ በቢሯው አገኘኋቸው፡፡ ያችን ቢሮ አልወዳትም. . . ለበርካታ ቀናት እየተጠራሁ ተንገላትቸባታለሁና እናደዳለሁ፡፡ ብቻ ምን ይደረግ ሳልወድ በግዴ ጉዳየን ጨርሸ መውጣት አለብኝ፡፡ ሰላምታ ከተለዋወጥን በኋላ ክቡር ዲፕሎማቱ ወደ ውይይታችን እንዲህ ሲሉ በጥያቄ ጀመሩት "...በር ላይ በሚገኙ ዜጎች ዙሪያ ያለህ አስተሳሰብ ምንድ ነው?" . . . በወፍራም መነጽራቸው ስር የሚያነጣጥረው አይናቸው ውስጤን ይረዳ አይረዳ ግን አልገባኝም . . . ብቻ ሰውየው በዜግነት ማጣራት ላይ በሚያደርጉዋቸው ጠበቅ ያሉ እርምጃወች ቅሬታ የሚያሰማባቸው ብዙ ቢሆንም እኔ ግን አንዳንዴ የሚወስዱት እርምጃ ከብርን ለማጠበቅና ለደህንነት እስከሆነ ድረስ መጉዋተቱ ብዙዎችን ቢያስተጉዋጉልም ይሁን በሚል ቅሬታ የለኝም፡፡ ከፖለቲካ ፍላጎታቸው ፤ ከረጂም ጊዜ የሥራ ልምዳቸው አንጻር የግለሰቦችን መቀመጫ ከማስጠበቁ በላይ በኢትዮጵያውዊነታቸው ለሚሰጡትን ክብር እንደሚገዝፍ የተረዳሁበት አጋጣሚ ነበርና ዘና ብየ የሆድ የሆዴን መናገሩን መርጫለሁ፡፡ የባለስልጣኑ አቀራረብ እጂግ በጣም በተለሳለሰ ነበርና እንደዜጋ የሚሰማኝን እንደ ባለሙያ ማድረግ

**pdfMachine**
**A pdf writer that produces quality PDF files with ease!**
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, simply open the document you want to convert, click “print”, select the “Broadgun pdfMachine printer” and that’s it! Get yours now!

ያለብኝንና ያደረግኩት ለማስረዳት ሞከርኩ፡፡ በምሰጠው ሙያዊ ትንታኔ አንዳዴ ጣልቃ እየገቡ እርሳቸው አስተያየታቸውን መስጠት ቀጠሉ፡፡ ለውይይቱ ያመች ዘንድ በተለያዩ አጋጣሚዎች በኢትዮጵያውያን ዙሪያ የማቀርባቸውን ዘገባዎች ላይ መነጋገሩ ለመግባባት ብቸኛ አማራጭ መሆኑን ስለተረዳሁ በዚያ ዙሪያ እንድንነጋገር ጠይቄያቸው መነጋገር ጀመርን፡፡ ዘገባዎችን እንደሚከታተሉና በአንብዛኛው "ወግ ለምጣፈጥም ይሁን ሆን ብለህ በነገር ሸንቆጥ ታደርገናለህ" የሚል አስተያየታቸውን አከታትለው ሰነዘሩ፡፡ በተለይም ከቅርብ ወራት ወዲህ በድልድዩ ስር የወደቁትንና በአሁኑ ሰአት በቆንስሉ በር የወደቁትን ዜጎች ጉዳይ በሚመለከት የማቀርባቸው ዘገባወችን "የተዛቡና የተጋነኑ " መሆናቸውን ባለስልጣኑ ገለጹልኝ፡፡ እኔም በሚቀርቡ ዘገባዎች ቅሬታ ካላቸው ቅሬታውን በነጻነት ለማስተናገድ ሁኔታወችን እንደማመቻችላቸው ያም ሆኖ ተጋነኑ ስለሚባሉት በአይኔ ያየሁትን ከፎቶና ከድምጽ መረጃ ጋር የተጠናቀሩ ለመሆናቸው ለማስረዳት ሞከርኩ፡፡ አንድ ሰአት ገደማ በፈጀው ውይይታችን በዚህ ዙሪያ ነገሮችን እያነሳን ብንጥልም የሚቀርቡ ዘገባወችን በጥንቃቄ እንድሰራ ለሰጡኝ ምክር አመስግኘ ተለያየን፡፡ ከባለልጣኑ በር በወጣሁበት ቅጽበት የተፈጠረው ግን እጅግ አስደንጋጭ ክስተት ነበር፡፡

## የመጨረሻው አማራጭና ሰቆቃና ብሶት የወለደው ቀቢጸ-ተስፋ

ከአምስት ቀናት ደጂ ጥናት በሁዋላ የቆንስሉን በር በሃይል ገፍትረው በመግባት ለጥያቄያችን መልስ ይሰጠን በሚል የቆንስል መስሪያ ጋር አለመግባባት የፈጠሩት ኢትዮጵያውያን ስደተኞችና የጂዳ ቆንስል መስሪያ ቤት ውዝግብ ልዩ ጥበቃ እስከ ማስጠራት ያደረሰውን አጋጣሚ ታዘብኩ፡፡ በሁኔታው ግራ የተጋቡት ዲፕሎማቶች ልዩ የዲፕሎማቲክ ጠበቃ ጉዋድ ሃላፊ በማስጠራት ወታደሮች ግቢ ገብተው ኢትዮጵያውያኑን ያወጡዋቸው ዘንድ ትዕዛዝ ሰጡ፡፡ የልዩ ጥበቃው ሃላፊዎች "ወደ ቆንስሉ ግቢ አንገባም ሁኔታውን ለማረጋጋት ሞክሩ" ሲሉ መከሩ፡፡ ቆየት ብለው ጉዳዩ ያጤቡት ባለስልጣናትና የልዩ ጥበቃው ሃላፊ ጥንቃቄ የተሞላበት መልስ በመስጠት ታዕዛዙን ተግባራዊ አለማድረጋቸው ትልቁ ችግር ከመምጣት ገታው፡፡. . . ከቀድሞው አስዎጡልን ሃሳብ ራሳቸውን ስበው አፍጮሌ ካድሬዎችን መጠቀሙን እንደ መልካም አማራጭ የወሰዱት ዲፕሎማቶች ሁኔታውን ለማብረድ መስራት ይዘዋል፡፡ ከቅርብ ርቀት ሆኘ ጉዳዩ ስከታተል በቆንስሉ ጽህፈት ቤት ሃላፊ የሆኑ በጂዳና አካባቢው የህዎሃት ከፍተኛ ባለስልጣን ጋር አይን ላይን ተጋጨን ፡፡ ፊታቸው ተረብሿል. . . በ መለሎው ቁመታቸው ላይ ያደረጉት ነጣ ያለ ቡናማ ሱፍና ከረባት ግርማ ሞገስ ችሯቸዋል፡፡ ደም በጎረሰና በተበሳጨ አይናቸው ገላመጡኝ . . . ምክንያታቸው አልገባኝምና ምን አጠፋሁ በሚል አይነት ከሚገለምጠኝ አይናቸው ጋር የተጋጨ አይኔን አቁለጭልጨ መልስ ተመጸንኩ፡፡ ብስጭታቸውን በሚያስረዳ መንገድ ፊታቸውን ዘወር አድርገው ወደ ቢሮዋቸው ተመለሱ፡፡ ሳላነጋግራቸው መሄድ አፈለግኩምና ወደ ቢሯው አመራሁ . . .  የሉም፡፡ የት እንደሄዱ ከፊት ለፊቴ ያገኘሁትን ሰራተኛ ጠየቅኩና ወደ ቆንስሉ ጀኔራሉ ቢሮ መሄዳቸው ተነገረኝ፡፡ ወደዚያው ተከትያቸው ሄድኩ ፡፡ በሩ ዝግ ነው . . . ካሜራ የተገጠመለትን በር መጥሪያ ደጋግሜ ነካሁት . . . የሚከፍተኝ አጣሁና ተመልሸ ገርግሩን መታዘቤን ቀጠልኩ፡፡ በዚህ ሁኔታ ላይ እያለሁ በቪዲዮ ካሜራ የሚጠበቀው የአምባሳደሩና የባለስልጣቱ ቢሮ ነገር ግራ አጋባኝ፡፡ በሩ ያለ ባለጉዳይ መግባት በሚል ማስታወቂያ ተለጥፎበታል . . . ችግር ያለበት ወደ ባለስልጣናቱ ለመድረስ በሩ በካሜራ ታጥሯል ! ይህ በመሆኑ እንደ ድሮው የአሰራር ችግር ሲከሰት ፤ ነዋሪው በደሉን የሚቀርፍለት ሲያጣ ወደ ዋና ሃላፊው ዘሎ መግባትና ችግርን አስረድቶ ማስፈጸም አሁን ብዙም የለም፡፡ የባለስልጣኑ በግቢው የወደቁትን ችግረኞች እንዳያዩ መግቢያ በራቸው ከህዝቡ መግቢያ ይለያል. . . ይህን ጉዳይ ከማውቀው ብዙ ጊዜ የተቆጠረ ቢሆንም አስተውየው ግን አላውቅም ነበር፡፡ ህዝባዊ ግልጋሎት እንዴት ነው የሚሰጠው ? ህዝባዊ ግልጋሎትን ሰጭና ተገልጋዩ እንዲህ መለያይት አለባቸው? ወይስ እኔ እየተፈላሰፍኩ ነው ? ስል ራሴን ጠየቅኩ !መልስ ግን የለኝም! . . . እኔም በማቀርብቸው ተደጋጋሚ ዘገባወቸ ዙሪያ ለመነጋገር  በጂዳ ቆንስል የዜግነት ደህንነት ሃላፊ ቢሮ እግሬን ስነቅል የተከሰተው ድንገተኛ ሁኔታ ለራሴ አግራሞትን ፈጠረልኝ ፡፡ ከረፋድ እስከ ቀትር ለሰአታት የቆየውን አሰጣገባ በአይኔ በብሌኑ ተመለከትኩ ፡፡ ከሰአታት ውዝግብ በኋላ በካድሬዎች ሺምገላ የቆንስሉ ዲፕሎማቶች ለአቤቱታ አቅራቢዎች ክትትልም እንደሚደረጉ ቃል በመግባታቸው ኢትዮጵያውያኑ ከቆንስሉ በር እንዲለቁ በመደረጉ ወደ ነበሩበት ድልድይ አመሩ፡፡

በተገባው ቃል መሰረት የቆንስሉ የዜጎች ደህንነት ሃላፊ ለመጀመሪያ ጊዜ እቦታው ድረስ ሄደው ዜጎችን ጎበኙ፡፡ ባለስልጣኑን ተከትሎ የቆንስሉ ጉዳይ ፈጻሚ በተማሳሳይ ሁኔታ ጉብኝት ተስፋ ሆነና ነዋሪዎች ትንፋሻቸውን መሰብሰብ ችለዋል፡፡ ነዋሪዎች ቦታውን በለቀቁ ማግስት "ጀዋዛት" የሚባሉት የፓስፖርት ፖሊሶች በቆንስሉ አካባቢ መጥተው እንደነበር ተሰማ፡፡ ነዋሪዎችን ሊወስዱ መጡ መባሉ ለመያዝ ፈልገው

**pdfMachine**
**A pdf writer that produces quality PDF files with ease!**
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, simply open the document you want to convert, click “print”, select the “Broadgun pdfMachine printer” and that’s it! Get yours now!

ወደ ድልድይ የተባረሩትን ነዋሪዎችን ግራ አጋባ፡፡ ይህ በሆነበት አጋጣሚ ወደ ቆንስል መስሪያ ቤቱ በመደወል ያገኘሁት መረጃ ግን ከተባለው መረጃ ጋር ይለያል፡፡ የወታደሮቹ አመጣጥ በቆንስሉ በር ላይ ዜጎችን ለመያዝ ሳይሆን በዜጎቹ ዙሪያ ላይ ለመነጋገር መሆኑን ተረዳሁ፡፡ የሮመዳን ጸሎት ገብቷል፡፡ የት መረጃው እንደሚገኝ ባይገባኝም ከፍጉን ዜጎችና ከተለያዩ አቅጣጫዎች የማገኘው የትክክለኛ መረጃ ፍሰት ፍጥነት እያስደመመኝ መጥቷል፡፡ በሮመዳን ዋዜማ ለወር ያህል ከአካባቢው ያልነበሩት አምባሳደሩ የመምጣታቸውን ዜና ከግፉአኑ ሰማሁ፡፡ በገባ ማግስት በዚህና በቆይየው ችግር የተሰላቹት ነዋሪዎች በበነጋው ወደ ቆንስሉ ለሌላ ዙር አቤቱታ መጡ፡፡ ነዋሪዎችን ለመጀመሪያ ጊዜ በአካል ያገኙት የጂዳ ቆንስል መስሪያ ቤት አምባሳደር ተክለአብ ከበደ ዜጎችን በቆንስሉ አዳራሺ በመሰብሰብ ያለውን አማራጭ አቀረቡ ፡፡ ቀጥለውም የነዋሪውን ብሶት ካዳመጡ በኋላ መንግስታቸው ችግሩ ለመፍታት ጥረት እያደረገ መሆኑን አስረዱ፡፡

ለአቤቱታ የመጡትን ሁሉንም ነዋሪዎች በቡድን በቡድን እንዲለዩ አዘዙ ፡፡ በሺተኞችና አቅመ ደካሞችን ከተቀሩት እንዲለዩ ተደረገ ፡፡ ቲኬት ከፍለው መሄድ ለሚፈልጉና አማራጩ እንዳለና እስኪሳፈሩ ድረስ የሚቆዩበት መጠለያ በቀን አስር የሳውዲ ሪያል መክፈል ከቻሉ የሳውዲ መንግስት ጊዜያዊ መጠለያ ማዘጋጀቱን ገለጹ፡፡ ለመጠለያና ለምግብ የሚሆን ገንዘብ ጨረስን ብለው ወደ ሃገር መግባት ለሚፈልጉ ነዋሪዎች ይህ የተሻለ አማራጭ ነው ሊባል ባይችልም እንደ አማራጭ የተገኘው ይህ ብቻ ነው ፡፡ አብዛኛው ነዋሪ በየአንባሳደሩ የቀረበው አማራጭ ባያስደስታቸውም  ከዚህ በፊት ቀርቦ የማያውቅ የተሻለ ምርጫ በመሆኑ ነዋሪው ማጎምጎሙን አቁሞ የየግል ውሳኔውን መውሰድ ካለበት አቁዋም ላይ  ደረሱ፡፡ እናም የቻለ ተበዳድሮ ገንዘብ ለመፈለግ ወደ ዘመድ ጉዋደኛን ደጅ መጽናት ሊኖርበት ነው . . . ያልቻሉ ራሳቸውን እንደሚሆን አድርገው ያልፈለጉትን ሆነው ይህን የጭንቅ ቀን መግፋት አለባቸው . . . በዚህ ሰአት ያነጋገርኩዋት አንዷት እህት አንገቷን ደፍታ የሚያማምሩ አይኖቿ በእንባ ተሞልተው ያጫወተችኝ ግን ፍጹም አይረሳኝም ". . . እስከዛሬ የስራው እንግልት ቢበዛብኝት ራሴን ሳላስደፍር በክብር ኖሬያለሁ፡፡ ክብሬን ከማጣ ብየ በድልድይ ስር ደፋ ብየ ከ እህቶቸና ከወንድሞቸ ጋር ኖሬ ወደ ሃገሬ የምገባበትን ጥሩ ቀን ብጠብቅም ጠሞብኝ ቀኑ አልመጣ አለ ! ዛሬ የተሰጠን አማራጭ ጥሩ ቢሆንም የተባለውን ገንዘብ ማግኘት ለማንችለው አማራጭ የሚሆን አይደለም. . . ይህ ያልጠቀመኝን ሰውነትና ደምግባቴን አይተው የሚጎነትሎኝ አሰሪዎቸም ሆኑ የባሎቻቸው ትወስድብናለች ብለው የሚፈሩ ሚስቶቻቸው ስራ ሊያሰሩኝ አልቻሉም . . . በዚህ አይነት ሁኔታ ከምሰራው የማልሰራው ይበልጣል፡፡ ስራ መስራት አልቻልኩምና ቤት ኪራይ ባለመክፈሌ የገዛ ጉዋደኞች ከቤታቸው እንድወጣ ፊት ነሱኝ . . . እረፍት ሰወጣ ፔፕሲ ይዘው የሚመጡ ለጉዋደኝነት የሚጠይቁኝ ያገሬ ልጆች የሚታመኑ አልሆኑም፡፡ ካንድ አይጸኑም ፡፡ አንዱዋን እዚያ አንዱዋን እዚህ ይወሽማሉ፡፡ በሺታው ደግሞ ሰውን እየጨረሰው ነው ፡፡ በዚህ ሁኔታ መወሸሙን ደግሞ ፍጹም አልወደውም፡፡ በዚህ ሁኔታ ጥያቄያቸውን ማሙዋላት ስለማልችል የሁሉም ተጠቂ ሆኛለሁ፡፡ አሁን ግን ሁኔታወች ተቀያይረዋል፡፡ አልቻልኩም ፡፡ ክብሬን ገስሸም ቢሆን የተገኘውን አማራጭ ሁሉ ለመጠቀምና ቀን ገፍቶ የናፈቅኳቸውን ቤተሰቦቸን ማግኘት አለብኝ፡፡ ሰው የፈለገውን ያህል ቢቸገር እንዴት ክብሩን ይሸጣል እል ነበር . . . ዛሬ ግን ክብራቸውን ዝቅ አድርገው በየመሸታ ቤቱ በቀይ መብራት ከሚደምቁት እህቶቸ ጀምሮ በየአውራ መንገዱ ተደርድረው ኑሮን በብልሃት የሚገፉ እህቶቸን ይቅር በሉኝ ማለት ይዣለሁ፡፡ ለክብራቸው መሸጥ ከጀርባቸው ያለውን ተራራ የሚያክል የማይገፋ ችግር ነው ከሚል ደርሻለሁ፡፡ ይህ ነው ሃቁ . . . ብቻ ፈጣሪ ይርዳኝ! " ይህች እህት በግልጽ ታጫውተኝ እንጂ ይህን መሰል መንገድ የተከተሉ በርካታዎች ለመሆናቸው ጥርጣሬ የለኝም፡፡ በዚህ ሁኔታ ሁሉም ተስፋ ቆርጧልና የየራሱን አማራጭ ለመውሰድ ወስኖ ከጾሙ ጋር ንዳድ በበዛበት አየር የሚገፋው የድልድዩ ኑሮ የሚሆን አይደለምና በአንባሳደሩ በቀረበለት አማራጭ እየቆዘመ ሁሉም በየአቅጣጫው ተበተነ፡፡ ፡

## ማን ቀረ . . . ? መሔጃ መድረሻ ያጡና የዓእምሮ የተነደፉ ግፉአን፡

ወደ ተለመደው ድልድይ አቀናሁ፡፡ ሁሉም በመሰለው ሲሰማራ መጠጊያ አጥተው ድልድዩን ተገን ካደረጉት ከሃያ እስከ ሰላሳ ከሚጠጉት ኢትዮጵያውያን መካከል አንዷት የሰባት ወር ነብሰ ጡርን ጨምሮ አንድ ወድና አንዷት ሴት ልጅ እግር የአዕምሮ ሁከት ያጋጠማቸው ይገኙበታል፡፡ ሲያዩዋት የምትፍለቀለቀው ይህች እህት ጥቁሩን አበያ ከላይዋ ላይ አውልቃ ከበሮ ትደልቃለች፡፡ ሌላው በተመሳሳይ የአእምሮ እክል የተዳረገ ኢትዮጵያዊ ወጣትን ወንድም ደግሞ ከኢትዮጵያውያን የሚያሸሽ አባዜ ተጠናውቶታል፡፡ ስቀርበውና ላነጋግረው ስሞክር ይሸሸኛል ፡፡ ይሄዳል እከተለዋለሁ . . . ምንም ማድረግ አልቻልኩምና የሱን ነገር ልቤ በሃዘን እንደተሰቀዘ ተውኩት . . .

**pdfMachine**
**A pdf writer that produces quality PDF files with ease!**
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, simply open the document you want to convert, click “print”, select the “Broadgun pdfMachine printer” and that’s it! Get yours now!

ከተቀሩት ጋር ያለችው እህት ግን አትሸሽምና ቀርቤ ሁኔታውን መታዘብ ፎቶ ማንሳትና ለማነጋገር ሙከራ አደረግኩ፡፡ በድልድዩ ታዛ በፕላስቲክ ቤት ሰርታ ትዘፍናለች ፤ ትዳንሳለች፡፡ ሲላት አንገቷን አቀርቅራ አይኖቿዋን ከብለል ከብለል እያደረገች በቆረጣ ስታይ ልብን በሃዘን ትሰብራለች ፡፡ የልጂነት ትክለ ቁመናዋ የጠራው ፊቷና በመቀስ ባይመስልም የቆረጠችው በውል ያልተከረከመው ጸጉር ከፍና ዝቅ ብሎ እዚህ እዚያ ጉች ጉች ብሎ ቢታይም አተከከሉ ሰንደዶ ለመሆኑ የተሞነጫጨረው ተልባ የመሰለው የጸጉር ዛላ ይመሰክራል፡፡ . . .ብቻ አልፎ አልፎ ዝምታ ታበዛለች . . . ሲላት እንዳልኳችሁ የሚያማምሩ ከንፈሯን ፍልቀቅ እያደረገች አስደንጋጭና በስራት በተደረደሩት ወትት የመሰሉ ጥርሶቿ ማራኪ ፈገግታዋን ትናኝበታለች፡፡ "ብዙ ጊዜ አይከፋትም ! ደስተኛ ናት ! አልፎ አልፎ ደግሞ ሌላ ሰው ትሆናለች . . . ዝም ትልና ታለቅስልች. . . እንባዋ አያቋርጥም . . . ታንዶለድለዋለች ..." ይህን ያጫወተኝ እዚያ ድልድዩ ስር ከሱዋ ጎን የከረመ ምስኪን ወንድም ነው፡፡ ሰላም ስትሆን . . . ውላ ከምታድርበት አለም ስትነቃ ፤የምታወራው የልጂነት ትዝታ ፤ የጥቁር አንበሳ ትምህርት ቤት የሞቀ የደመቀ የወጣትነት ህይወት፤ የደራ የሞላላቸው ቤተሰቦችዋ ፤ፍቅራቸው የሚያሳሳ ወንድሞችዋ እንክብክቤብና የሷ "አዱ ገነት" ሌላ ናቸው ሌላ ናቸው፡፡ ብቻ ይህን የምታወራው ጨለማን ተገን አድርጋ ያው ቀለል ሲላት ብቻ በመሆኑ አልተመቸኝም፡፡ ሰላም ነው ብየ የሱዋን ወግ ላዳምጥ ደጋግሜ ብሄድም አንዴ ዝም ብላ ብቻዋን እየሳቀች እየተፍልቀለቀች ሌላ ጊዜ አኩርፋ አገኛትና ተበሳጭቸ እመለሳለሁ፡፡. . . ወደ ስራ ስሄድ ሳገድም ነቅታ አግኝቸ የሰማሁትን ከራሱዋ አንደበት አዳምጠዋለሁ በሚል ብዙ ደከምኩ፡፡ አንድ ቀን ግን ተሳካልኝ . . . ከቅርብ ርቀት ቁጭ ብየ እየተፍለቀለቀች ስታወጋኝ መታመሙዋን ረሳሁት፡፡ መጠየቅና መልስ ማግኘት የለም . . . ብቻ በይ ሲላት የምትጀምረው ጨዋታዋ ምራቅ ያስውጣል፡፡ ሙሉም ባይሆን እየቦጫጨቀች ከምታቻውተኝ ማንነቱዋን አንድ ጫፍ እንድረዳ አድርጎኛል፡፡ ከአብዮት አደባባይ እስከ ቦሌ ባለው ሰፈር የት ተወልዳ እንዳደገች ከአንደበቷ ለመስማት ግን አልቻልኩም. . . አሁንም ያለችው እዚያው ነው ፡፡ ከቅርብ ርቀት ካርቶችን ወደ ሃገሩ ለመሄድ ፈልጎ ከእርሷው ጋር ኑሮ ያጎራበተው ወንድም ቀንና ማታ ከወሮበላ ይጠብቃታል፡፡ ወንድሜ ያያታል ይሰማታል እንጂ መንካት አይችልም፡፡ አግድማ እንዳትሄድ ይጠብቃታል፡፡ አንዳንዴ ይጋጫሉ አንዳንዴ ይስማማሉ፡፡ ተጎራብታዋለችና ስትደሰት ስታዝን ስትከፋ ስታወራና ስትስቅ ምግቡ ሆኖ ያጠግበዋል፡፡ በዚህ ሁኔታ ከቀን ቀን ሲገፋ ምስኪን ወንድሜም በዚያ ችግር ላይ እያለ በፍቅሩዋ ይጠለፍ ይደምቅም ይዟል . . . ብዕራቸው የተባ ጸሃፍትን ያላዩት ድንቅ ታሪክ ቢሆንም አቅሙ ያለው በአካባቢው አይታይም፡፡ ቢኖርም መድፈሩ ልብን ይጠይቃልና ታሪኩን በሰሚ ሰሚ መስራት አይቻልምና ሁኔታወች እንደጎረበጡ ነግቶ ይመሻል፡፡ አነሰም በዛ እንደ ጋዜጠኛ በጨረፍታ ለማሳየት ያደረግኩት ሙከራ ላንባቢዎቸ በትክክል ከደረሰ መልካም ነው፡፡ የዚህች እህቴ መከራ የዚህ ዘመን የኢትዮጵያውያን የአረብ ሃገር ህይወት ቁልጭ አድርጎ በማሳየት ለአቅመ አዳም ሳይደርሱ ለስደት የሚዳረጉ እህቶቻችን የተደበቀ እውነት ቁልጭ አድርጐ ያሳይል ከሆነ የልቤ ደርሷል፡፡



አዎ ! ጀሮ ላለው መስማት ያለበት እውነተኛ ታሪክ ብዙ ነው፡፡ ለቀረነው የአረብ ሃገር ስደተኞም ሆነ የአረቡን አለም ኑሩ ለመቀላቀል ቋምጠው ለተነሱት አስተማሪ ነውና ተጨማሪ መረጃወች መሰባሰቤን ቀጥያለሁ !

## የሚጠበቅ ግን . . . ሳይታሰብ የመጣ አደጋ !

በድልድይ ስር ተገኝቸው ዜጎች ደረሰብን የሚሉትን በደል ለመረጃ ፍጆታ በመቅረጸ ድምጽ ለአቃቅሜ ሳልጨርስ ከወትሮው የተለየ ነገርን ተመለከትኩ፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ በድልድይ ስር የሚገኙ የህንድ የፓኪስታን የሲሪላንካ የባንድላዲሺና የተለያዩ ሃገር ዜጎች ከኢትዮጵያውያኑ ጋር ቃለ መጠይቁን ሳደርግ ከበውኛል፡፡ ሰው ሲበዛ ለመሄድ በመዳዳት ላይ እንዳለሁ የሳውዲ የተለመደ አለባበስ ነጭ ቶፕ ቀይ ጥምጣምና ከመካከል ላይ የምትደረገውን "ቁድራ" እያሉ የሚጠሩዋትን ጥቁር ክብ ገመድ ቢጤ ያጠለቁ ነጭ ለባሽ ያገሩ ሰወች መሆናቸው አልጠፋኝም፡፡ ለሁሉም እጀን ቀስ አድርጌ ኪሴን ዳሰስኩ፡፡ የጋዜጠኝነት መታወቂያና የፍቃድ ደብዳቤየ መኖር አለመኖር ዳሰስኩና መኖሩን ስረዳ ተረጋጋሁ፡፡ ጸጉረ ልውጥ አረቦች "በሲቪል" መኪና ላይ ቀልጠፍ ቀልጠፍ በለው ወረዱ፡፡ ወጣቶች ናቸው፡፡ "አንተ ማነህ? ምን እያደርግክ ነው?" እና ሌላም ሌላ ጠየቁኝ፡፡ ከሁሉም በፊት መታወቂያቸውን እንዲያሳዩኝ ጠየቅኩ፡፡ አንዱ ዘወር አድርጎ

**pdfMachine**
**A pdf writer that produces quality PDF files with ease!**
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, simply open the document you want to convert, click "print", select the "Broadgun pdfMachine printer" and that's it! Get yours now!

አሳየኝና ተግባባን፡፡ እኔም በበኩሌ ማንነቴን አስረዳሁና መታወቂያየን አሳየሁ፡፡ የመጣሁበትን አላማ ከገለጽኩ በኋላም ቢሆን ፎቶ በማንሳቴና ድምጽ በመቅረጼ ዙሪያ ጠንከር ያለ ፍጥጫ መፈጠሩ አልቀረም፡፡ ብዙም እንግልት ግን አልደረሰብኝም፡፡ የክትትሌን ዋና አላማ ፤ የምሰራበት ራዲዮ መታወቂያና ለሳውዲ ማስታወቂያ ሚኒስትር የተጻፈልኝን ደብዳቤ ጭምር አሳይቻቸው ነገሩ ለዘብ አለ፡፡ ከሁሉም በላይ እስኪጣራም ቢሆን በቁጥጥር ስል እውላለሁ የሚል ስጋት አድሮብኝ በተንቀሳቃሺ ስልኬ በአስቸኳይ የላኩዋት መልዕክት በቦታዋ ደርሳ ነበርና ድጋፍ የሚያደጉልኝ ወገኖች ደረሱ፡፡ ብዙም ሳይቆይ ነገሩ በሰላም ተፈትቶ ከገባሁበት ማጥ ወጣሁ. . . እኒህ ወገኖች በቀጣይነት ኢትዮጵያውያን ዜጎችን ለመርዳት ያደረጉትን ተጠቃሺ እርዳታ ዜጎቹን ለመጠበቅ ከተቀመጡት የሃገሬ ተወካዮች ጋር ሳወዳድረው ግራ እጋባለሁ . . . ለሁሉም የእጃቸውን ይስጣቸው ከማለት ባለፈ ምን ማለት አይቻልም ! . . . ባይሆን ሌላ ቀጠሮ እንያዝ !

## ቅዳሜ / ጥቅምት 6. 2003

መጣጥፌን አጠናቅቄ የፊደል ግድፈት ቢኖርበት እባክህ ገረፍ ገረፍ አድርገው ብየ ለወንድም ሲራጂ ለእርማት ሰጠሁት ፡፡ ከላይ እስከ ታች በስሜት አንብቦ ቢጨርሰውም የፊደል ግድፈቱን ከመንገር ይልቅ የዚህችን ጉብል መዳረሻ የት እንደሁ ጠየቀኝ ፡፡ ድልድዩ ስር አልኩት . . . እንደ መቆዘም ሲል ማየት ከፈልግክ እንያት አልኩትና ወደ ዚያው አቀናን ይህ የሆነው ያሳለፍነው ቅዳሜ ጥቅምት 6. 2003 መሆኑ ነው ፡፡ ወደ "ከንደራ" ተብሎ ወደሚጠራው ድልድይ አመራን ፡፡ ዛሬ በተራቸው የተለያዩ ዜጎች የድልድዩን ስር ሞልተውታል፡፡ እንደ ቀድሞው ብዙ ሃበሾች የሉም . . . ጥቂት እንደተራመድን ያ ይሸሻል ያልኳችሁ የአዕምሮ ሁከት ያጋጠመው ልጅ እግር ሃበሻ ወጣት ወንድምና ያች ጉብል መኖራቸውን መኪና የሚያጥቡ ሶማሌዎች ነገሩን፡፡ ብዙም ሳንቆይ ልጁ ያለበትን ቦታ አመላከቱን፡፡ ወጣቱን የአዕምሮ በሺተኛ አግኝተን ለማነጋገር ብንሞክርም ዛሬ ብሶበታል . . ይሳደንብም ጀምሯል እኔ ሳውቀው እንዲህ አያደርገውም ነበር ". . . እዚህ ወግዱ ጥፉ ! ሂዱልኝ . . . ምን ትፈልጋላችሁ ? !" እያለ ይሸሽን ገባ . . . እያዘንን ከፊቱ ራቅን ፡፡ ወንድሜ ሲራጅ ሊያም አልቻለም. . . ግን ማመን ግዴታው ነው ! ሲራጅ አካሉ አብሮኝ ይሁን እንጂ በሃሳብ ከኔ ጋር ያለ አይመስልም. . ! " ፊቱ ተለዋውጧል ! . . . አልፎ አልፎ ሺበት ጣጣል ያደረገውን ጎፈሬውን አንዴ አሸት አሸት እያደረገ የሚጨብጠው ያጣ አስመስሎታል. . . ይቆይና አንድ እጁን በሆዱ ለጥፎ ቀኝ እጁን ደገፍ አድርጎ በጣቶቹ ደፉ ያደረገው ፊቱን እንደ መያዝ አድርጎ ጣቶቹን እየቀያየረ በአፍንጫውና ፊቱ አግድም እየያዘ ይለቃቸዋል. . . ዝም ይልና ደግሞ በትካዜ በአግራሞትና በሃዘን  አካባቢውን ይቃኛል . . . የዚያችን ጉብል ቀራቅንቦና ኮተታ ኮተት እዚያው አለ . . .  የተቦጫጨቀ ሻንጣዋ . . . አንድ እግር ነጠላ ጫማ ፤ አንድ እግር የወንድ አሮጌ ጫማ በወዝ የጠገበ የተቀዳደደ ጨርቅ. . . ፕላስቲክ ምኑ ምናምኑ ወደ ተደረደረበት ይመለከታል ! . . . በወረቀት ላይ ያየውን ቦታ በአይኑ ቢያይም አዕምሮዋ ታውኮ ከበሮ ትደልቃለች ብየ ያስነበብኩትን እህት ማየት አልቻለም ! ማየት ቢችል ደስ ባለኝ ነበር . . . ዛሬ ያ ጠባቂዋ ወንድሜ የለም መሰል እንዳሻት ትዞራለች. . .  እኔም የሲራጅ ወድንሜ አግራሞት ዳግም እንዳዝን አስገድዶኝ ወደ መኪናችን ገብተን ወደ ቤታችን እስክንደርስ በሃዘን ድባብ ተውጠን ነበር ማለት እችላለሁ ! ብቻ ስንለያይ ልባችን ተሰብሮ እንደዋዎል ከማለት ውጭ ከፉም ሆነ ደግ ሳንተነፍስ በሰላምታ ብቻ ተለያየን ! . . .

እሁድ በማለዳው ልጆቸን ትምህርት ቤት እንዳደረስኩ ወደ ዚያች ጉብል አመራሁ፡፡ አገኘኋት . . . ስትዞር ውላ ይሁን አመሻሹ ላይ ምን እንደገጠማት አላውቅም ደክሟት ጧ ብላ ተኝታለች፡፡ አሁንም ያ ጠባቂዋ ወንድም የለም . . . ብዙም ሳልቆይ ወደ ስራየ ሳቀና ትምህርት ቤት ያገኘሁት የቆንስል መስሪያ ቤት ሰራተኛ የሰጠኝ ተስፋ ከተሳካ እሰየው ነው ስል ከራሴ ጋር እያወራሁ መንገዴን ቀጠልኩ ፡፡ የጠዋቱን መልሸ ማስታወስ ያዝኩ. . . ልጆቸን ትምህርት ቤት አድርሸ ልመለስ ስል ጉዳይ ፈጻሚ ወንድሜ አገኘሁትና ከወራት በፊት በድልድይ ስር አብረን ስላየናት እህት አሁን ድረስ መኖር ገለጽኩለት፡፡ በአግርሞት መለሰልኝ ! አዎ . .. ስራ በዝቶበት ብቻውን እዚህና እዚያ ሲከላተም የሚጮሁበትን እንጂ የማይጮሁትን ማስታወስ አይችልም ይሆናልና ዘንግቷታል . . ." ፎቶዋን ለምን አትሰጠኝም? እባክህ ስጠኝና እናሳፍራታለን አለኝ? " በሰጠኝ ተስፋ ተጽናናሁና በአዎንታ ተለያየን . . . ፎቶዋን ዛሬውኑ አሳትሜ ለመስጠት ቸኩያለሁ . . . ካለላትና ወደ ሃገሩዋ ትሄዳለች ! ካላለላትም እዚሁ ውሃ በልቷት ትቀራለች ብየ አላምንም ! ?. . . አልመኝላትምም . . . ! ለሁሉም እኔ ግን እከተላታለሁ . . . የመዳረሻዋንና የእጣ ፈንታዋን ነገር ከቀሩት የተደበቁ እውነቶች ወጋወጌ ጋር ዘናንቄም ቢሆን እስካሳውቃችሁ ድረስ ለዛሬ በዚህ ይብቃን . . .  ይቀጥላል . . .

ቸር ይግጠመን

**pdfMachine**
**A pdf writer that produces quality PDF files with ease!**
Produce quality PDF files in seconds and preserve the integrity of your original documents. Compatible across nearly all Windows platforms, simply open the document you want to convert, click “print”, select the “Broadgun pdfMachine printer” and that’s it! Get yours now!